## የክልሉ አጠቃላይ ገጽታ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በምዕራብ ሱዳን፣ በምስራቅ የአማራ፣ በሰሜን ሱዳንና የአማራ ክልል፣ በደቡብ የኦሮሚያ ክልልና ደቡብ ሱዳን የሚያዋስኑት ሲሆን የቆዳ ስፋቱ 51000 ስኩየር ኪ/ሜትር የሆነ፣ የሀገሪቱን 4.63 በመቶ ድርሻ የያዘ ነው። እንደ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ገ/ኢ/ል/ቢሮ ስነ ህዝብ የ2012 ዓ/ም የህዝብ ትንበያ መረጃ መሰረት የክልሉ ህዝብ ብዛት 1156999 እንደሆነ የሚገመት ሲሆን ከአገሪቱ ህዝብ 0.9 በመቶ አካባቢ ድርሻ ይይዛል። ከዚህ ውስጥ 578773 (50.02%) ወንዶችና 578226 /49.98%/ ሴቶች ናቸው። ከመኖሪያ አካባቢ አንፃር 824940 ወይም 71.3 በመቶ የሚሆነው በገጠር የሚኖርና ኑሮው በዋነኛነት በግብርና ላይ የተመሠረተ ሲሆን ቀሪው 332059 (28.7 በመቶ) የሚሆን ህዝብ በከተማ የሚኖር ነው። የህዝቡን የዕድሜ አወቃቀር ስንመለከት ዕድሜያቸው ከ14 ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት 22.02% ሲሆኑ እድሜያቸው ከ15-24 ዓመት የሆኑ ወጣቶች ደግሞ 19.55% ናቸው። ከጠቅላላ ህዝቡ ህጻናት 22.02%፣ ወጣቶች 19.55%፣ ሲሆኑ ከ15-64 ዕድሜ ያላቸው ደግሞ 54.48%፣ 65 አመትና እና በላይ የሆኑት ደግሞ 3.95% ናቸው። ይህ ከፍተኛ የሆነ የሴቶችና የወጣቶች ቁጥር መኖር የወሳኝ ኩነትን ምዝገባ ሽፋን በማሳደግ የሚደረገውን ሁለንተናዊ፣ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት ለማረጋገጥ ያስችላል። የክልሉ ህዝብ ጥግግት በአማካኝ 19.82 ሰው በስኬር ኪሎ ሜትር እንደ ሚኖር የሚያሳይ ሲሆን ይህም ዜጎች በምዝገባ ስርዓቱ በቀላሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያስችላል። ክልሉ በ3 ዞኖች፣ በ3 ከተማ አስተዳደሮች፣ በ1 ልዩ ወረዳና በ22ወረዳዎች እንዲሁም በ531 የምዝገባ ጣቢያዎች የተዋቀረ ሲሆን የጉሙዝ፣ የበርታ፣ የሺናሻ፣ የማኦ፣ የኮሞ፣ የአማራ፣ የአገው፣ የኦሮሞ፣ የጉራጌ፣ የከንባታ፣ ቅማንትና ሌሎች በርካታ የሆኑ ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች በአንድነት የሚኖሩበት ነው።